## Social: የተጣሉና ያገለገሉ ፌስታሎችን መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል

ኤስ.ኦ.ኤስ አዲስ ተፈጥሮን በማልማት ብክለትን ማስወገድ ማኅበር በመላ ሀገሪቱ ያገለገሉና የተጣሉ ፌስታሎችን እየሰበሰበ መልሶ ጥቅም ላይ ሊያውል የሚያስችል ፕሮጀክት በ72 ሚሊዮን ብር ለማቋቋም እንቅስቃሴ በማከናወን ላይ መሆኑን የማኅበሩ የሥራ ኃላፊዎች ገለጹ፡፡

ኃላፊዎቹ እንዳመለከቱት ማኅበሩ ከ25 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ወገኖች የሥራ ዕድል የሚያስገኘውን ይህንኑ ፕሮጀክት የሚያካሂደው በደብረዘይት ከሚገኘው ኦክስፎርድ ፖሊቲሊያን ኢንዱስትሪዎች ጋር በመተባበር ሲሆን ፕሮጀክቱም የሚቋቋመው በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ከሚገኘው ቆሼ በሚባለው አካባቢ ነው፡፡

በዚህም ሥፍራ አሮጌ ፌስታሎችን የሚያጓጉዙ ተሽከርካሪዎች ማቆሚያ፣ ፌስታል የሚያጥብና የሚያደርቅ፣ እንዲሁም መልሶ ጥቅምት ላይ የሚያውሉ መሳሪያዎች የሚተከሉ ሲሆን መንገድ፣ ውሃና ሌሎች መሰረተ ልማቶችም ይከናወናሉ፡፡

የፕሮጀክቱ ዝርዝር ለፌዴራልና ለአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣናት መሥሪያ ቤቶችና ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ኃላፊዎቹ ቀርቧል፡፡

ወይዘሮ ኪሮስ ወልደጊዮርጊስ የማኅበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ እንዳመለከቱት ፕሮጀክቱን በቆሼ አካባቢ ለማቋቋም ያስፈለገበት ምክንያት የአዲስ አበባ ደረቅ ቆሻሻዎች መጣያ ሥፍራ ስለሆነና ከዚህም ሥፍራ ያገለገሉ ፌስታሎችን እየለዩ ለማውጣት ያመቻል ከሚል እምነት ነው፡፡

ኅብረተሰቡ ደረቅ ቆሻሻዎችን ከየቤቱ በሚያስወግድበት ጊዜ ፌስታሎችን፣ ወረቀቶችን፣ ጣሳዎችንና ሌሎችንም በመልክ በመልካቸው በከረጢት ወይም በጆንያ ቢያስቀምጣቸው ዋጋ እንዳላቸው አስገንዝበዋል፡፡

ማኅበሩ ከሦስት ዓመት በፊት በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15/16 ለመጀመሪያ ጊዜ ያዘጋጀው የተጣሉ ፌስታሎችን የመልቀም ሙከራ ፕሮጀክት በአሁኑ ጊዜ ጥሩ ውጤት ማስገኘቱንም ሥራ አስኪያጂ ጠቁመው፣ በባዕታና በቅዱስ ገብሬኤል ቤተክርስቲያናት አካባቢ የሚገኙ አራት ቀበሌዎች በአንድነት በተጣመሩበት ቀበሌ 15/16 ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለው ይኸው የሙከራ ፕሮጀክት አሮጌና የተጣሉ ፌስታሎችን በመልቀም የሚተዳደሩ 30 ሴቶችን ማሰባሰቡን አስረድተዋል፡፡

ሴቶቹ የለቀሟቸውን ፌስታሎች ርዝመቱ 3 ሜትር ስፋቱ 3 ሜትር በሆነ ትልቅ የፕላስቲክ ከረጢት ውስጥ ያጠ ራቅሙታል፡፡ በዚህ አይነቱ የተጠራቀሙትን ፌስታሎች ደብረዘይት የሚገኘው ድርጅት ኪሎ አንድ ብር ከ50 ሳንቲም ሂሳብ እየገዛ ያጓጉዛል፡፡ ከዚህም ሽያጭ ውስጥ ለለቃሚዎች በኪሎ አንድ ብር ሂሳብ ሲከፍላቸው ሃምሳ ሣንቲሙ ደግሞ ተጠራቅሞ ለማኅበሩ ልዩ ልዩ ወጪዎች ይውላል፡፡ አንድ ለቃሚ በወር እስከ 400 ኪሎ ፌስታል ትለቅማለች፡፡ ለዚህም 400 ብር ይከፈላታል፡፡

የሌሎችም ቀበሌዎች ነዋሪዎች ይህንን ጥቅም በመገንዘባቸው እነሱም ዘንድ እንዲጀመር ጥያቄ እያቀረቡ መሆናቸውን ወ/ሮ ኪሮስ ተናግረዋል፡፡ ይሁን እንጂ ማኅበሩ በአሁኑ ጊዜ ቦታ፣ የሰው ኃይልና ገንዘብ ስለሌለው ጥያቄውን ለጊዜው ሊያስተናግድ አልቻለም፡፡ በይበልጥ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌዴራልና የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣናት መሥሪያ ቤቶችና የአራዳ ክፍለ ከተማ የዕርዳታ እጃቸውን እንዲዘረጉለት ማኅበሩ ብዙ ጊዜ ወትውቶ ነበር፡፡ ዕርዳታ አላደረጉም፡፡ ነገር ግን የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በአንድ ወቅት ለአንድ ፕሮግራም ማከናወኛ 5 ሺህ ብር መለገሱን አስታውሰዋል፡፡

በተለይም የአምባሳደር ሚስቶች ፌስታል የሚያጥብና የሚያደርቅ መሣሪያ ገዝተው ለመስጠት ቃል መግባታቸውን፣ ይህም ሁኔታ በመጀመሪያው የሚሊኒየም አከባበርን አስመልክቶ በሚካሄደው እንቅስቃሴ ላይ አዲስ አበባ ከፌስታል ቆሻሻ ነፃ ለማድረግ ማህበሩ መነሳሳቱን አስረድተዋል፡፡

ወይዘሮ ሙላቷ ኃይለሥላሴ የማኅበሩ የኮሚኒኬሽን ኮሚቴ አስተባባሪ በበኩላቸው እንደገለጹት ኤምባሲዎች፣ መያዶችና የሮታሪ ክለብ ለማኅበሩ መንቀሳቀሻ ዕርዳታ ለግሰዋል፡፡ ማኅበሩ አሁን እየተንቀሳቀሰ ያለው ከእነዚህ ድርጅቶች በተገኘው ዕርዳታ ነው፡፡

ማኅበሩ ከሌሎች ደረቅ ቆሻሻዎች ይልቅ የተጣሉ ፌስታሎች ለቀማ ላይ ያተኮረው ፌስታል አካባቢን የሚበክልና ቶሎም የማይበሰብስ ጠንቀኛ በመሆኑ ነው፡፡ ለሰው ብቻ ሳይሆን ለመሬት፣ ለአዝርዕትና ለከብትም ጭምር ጠንቅ ነው፡፡ ፌስታል ሳይበሰብስ ለብዙ ዓመታት ሊቆይ ይችላል፡፡

ወይዘሮ እምባአፍራሽ በርሄ የማኅበሩ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ምክትል ሊቀመንበር እንዳብራሩት በቀበሌ 15/16 ውስጥ

እየተካሄደ ያለው ፕሮጀክት የሚቆየው ለሦስት ዓመት ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ለቃሚዎቹ ራሳቸውን ችለው ይሰራሉ፡፡ ማኅበሩ ደግሞ ወደ ሌላ አካባቢ ይንቀሳቀሳል፡፡ በዚሁ ቀበሌ ብቻ ካለፈው ዓመት የካቲት ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ 14 ሺህ ኪሎ አሮጌና የተጣሉ ፌስታሎች ተለቅመዋል፡፡

በለቀማው ላይ የተሰማሩት ሴቶች ምንም መተዳደሪያ የሌላቸውና ከለቀማው ብቻ በሚያገኙት የገቢ ምንጭ ብቻ የሚንቀሳቀሱ ናቸው፡፡ እናቶች በለቀማ ሥራ ላይ ሲሰማሩ ልጆቻቸውን የሚያቆዩበት መዋዕለ ሕፃናት ወደፊት ለማቋቋም መታሰቡንም ከወይዘሮ እምባአፍራሽ ማብራሪያ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በታደሰ ገብረማርያም

Ethiopian Reporter Posted on Sunday, November 12 @ 12:01:11 EAT by staff